**ማስጠንቀቅያ/ያሉበትን ቦታ ለቆ መውጣት**

**እውነታዎች፡** የሲያትል ባለስልጣኖች፡ በሲያትል ኣንዳንድ ቦታዎች ለሚኖሩ ነዋሪዎች ቦታውን ለቀው እንዲወጡ የሚጠይቅ ትእዛዝ ኣውጥተዋል። ይህም ማለት፡ ኣደጋ ያለበትን ቦታ ሙሉ በሙሉ ለቆ መሄድንና ወደ ሌላ የተመደበ ልዩ ስፍራ መሄድን ሊያጠቃልል የሚችል ትእዛዝ ሊሆን ይችላል።

**ምን ማድረግ ያስፈልጋል:**

- ቦታውን ለቀው እንዲሄዱ ሲጠየቁ፡ ወድያውኑ ይውጡ። በመልቀቅያ ማስታወቅያ ላይ በዝርዝር የሰፈሩትን መንገዶች/ጎዳናዎችን ተከተሉ። በኣንዳንድ መንገዶች ላይ ምልክቶችና መመሪያዎች ሊለጠፉ ይችላሉ።
- ኣ ቋራጭ መንገዶችን ኣትውሰዱ ምክንያቱም ማለፍ የተከለከሉ ሊሆኑ ይችላሉና።
- ኣስፈላጊ ነገሮችን ብቻ ይውሰዱ ለምሳሌ - መድሃኒቶች፡ ኣንዳንድ ልዩ ምግቦች፡ የግል ኣስፈላጊ ነገሮች፡ ለህጻናት የሚያስፈልጉ ነገሮች፡ ልብሶች፡ ገንዘብና ኣስፈላጊ ዶኩሜንቶች/ወረቀቶች የመሳሰሉ ብቻ ይውሰዱ።
- ቤትዎን ለቀው ከመሄዶ በፊት በሮችንና መስኮቶችን በደንብ በቁልፍ ይዝጉ።
- ከተቻለ፡ ከቦታው ውጪ የሚኖር ሰው ለማዳ እንስሳዎችዎን እንዲጠብቅሎት ያድርጉ። ምክንያቱም ኣንዳንድ የመጠለያ ስፍራዎች፡ እንስሳት ለማስገባትም ሆነ ለማዳ እንስሳቱ በየቦታው ልቅ እንዲሄዱ የማይፈቅዱ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ምንም ዓይነት የመ ጓ ጓዥያ መንገድ ከሌሎት፡ ከጎረቤት ወይም ከ ጓደኛ እርዳታ ይጠይቁ። መ ጓ ጓዥያ ሊያገኙባቸው የሚችሉ ቦታዎች የተመደቡ ከሆነ ደግሞ በእግር ሊደረሱ የሚችሉ መሆናቸውንና ኣለመሆናቸውን ኣስቀድመው ያረጋግጡ።
- ኣደጋውን በሚመለከት ኣዲስ መረጃ እንዳለ ለማወቅ በቀጣይነት ሬድዮ ተከታተሉ ።
- ***ይህንን መልእክት ለመረዳት፡ ለማየትም ሆነ ለመስማት የማይችል የሚያውቁት ሰው ካለ፡ ኣባክዎትን መልእክትቱ ኣስረድዋቸው።***

**ጠቃሚ ዌብሳይቶች :**

http://www.ready.gov/evacuating-yourself-and-your-family